ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት መጋቢት 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 70



## “የኢህአዴግ እብሪትና ትዕቢት አገርንና ህዝብን የሚያጠፋ ነው”

### አቶ ግርማ በቀለ 33ቱ ፓርቲዎች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ

6

## ከቤንሻንጉል አማርኛ ተናጋሪ ዜጎችን በግፍ የማፈናቀሉ ተጠናክሮ ቀጥሏል

### -ጥቃቱ ህፃናትና አረጋውያን ላይም እየደረሰ ነው

5

## በአፋር የተከሰተው ርሃብ ተባብሷል

### -የሚቾች ቁጥር 22 ደርሷል

10

## ኢህአዴግ አድርባይነትን ከማጥፋት ራሱን ማጥፋት ይቀለዋል

4

## ርዕዮት ዓለሙ ሁለተኛ ዲግሪዋን እንዳትማር ተደረገች

ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ የርቀት ትምህርት እንዳትማር መከልከሏን የዜና ምንጮቻችን አስታወቁ፡፡ የርዕዮት አለሙ ቤተሰቦችም የዜናውን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡

ለፍኖተ ነፃነት የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ርዕዮት እንደማንኛውም እስረኛ ሁለተኛ ዲግሪዋን ለመስራት ህንድ አገር በሚገኘው የሂንድራ ጋንዲ ናሽናል

ኦፕን ዩኒቨርሲቲ አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅማ ብትመዘገብም ማረሚያ ቤቱ መጀመሪያ ከፈቀደ በኋላ ፖለቲካል ሳይንስ እንደምትማር ሲታወቅ ክልከላ

ወደ ገፅ3 ዞሯል

## የመንግስትን ዘር ማፅዳት ዘመቻ ማስቆም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው

2

ፍኖተነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡

ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

## ርእሰ አንቀጽ

# የመንግስትን ዘር ማፅዳት ዘመቻ ማስቆም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው

አንባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የጻፈው ግን የማያነበው፣ አስከብረዋለሁ የሚለው ግን የማያከብረው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት በአንቀፅ 32 ማንኛውም ኢትዮጵያዊም ሆነ በህጋዊ መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር የውጪ ዜጋ በነፃነት በመላ ሀገሪቱ የመንቀሳቀስ፣ የሚኖርበትን ቦታ የመምረጥ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

ሆኖም ኢህአዴግ አማርኛ ተናጋሪዎች በመረጡት አካባቢ የመኖር መብታቸውን ከልክሏቸዋል፡፡ ይህ አደገኛ የመንግስት አካሄድ በአፋጣኝ ካልቆመ በሀገራችንና በህዝቦቿ መልካም ግንኙነት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ መንግስት እየፈፀመው ያለው ይሄ ዘመቻ አንድ ዘር ላይ ያነጣጠረ እንደነሆኑ ከዘር ማጥራት ተለይቶ ሊታይም አይችልም፡፡

የዘር ማፅዳት በአለም አቀፍ ደረጃ ከሚያስጠይቁ መንጀሎቹ መካከል ይጠቀሳል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ እንደሚታወቀው በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ በአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ የሚደረግን ከአንድ ሀገር የማፈናቀልና የሰባአዊ መብት ጥሰት ማድረስን የሚጨምር ነው፡፡
ባለፈው አመት ከደብብ ክልል ሜንቻ ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ በሺዎች የሚቆጠሩ አማርኛ ተናጋሪዎችን ማባረር የጀመረው የኢህአዴግ መንግስት አሁን ደግሞ ከቤንሻንጉል ክልል በተለይም ከያሶ ወረዳ 25 ሺህ አማርኛ ተናጋሪዎችን ማባረር ተጀምሯል፡፡ በግዳጅ ለአመታት ከኖሩበት አካባቢ የሚባረሩት ዜጎች ድብደባ፣ ዝርፊያና ሌሎች ኢሰብአው ድርጊቶች የሚፈፀምባቸው ከመሆኑም በላይ በርካቶች ውድ ህይወታቸውን በማጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

ዜጎቹ የሚባረሩበት ምክንያት የሚኖሩበት አካባቢ ተወላጅ አለመሆናቸው ነው፡፡ ለውጪ ባለሀብቶች ያለስስት ከአንድ ከተማ በላይ ስፋት ያለው ድንግል መሬት የሚሰጠው የኢህአዴግ መንግስት ኢትዮጵያውያንን "የትውልድ ስፍራችሁ አይደለም" በማለት በግፍ ማባረሩ ዛሬም ኢትዮጵያን የሚመሯት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንድንከት የሚያስገድደን ሆኗል፡፡

ዜጎች በመረጡት የሀገራቸው ክፍል የመኖር ህገመንግስታዊ መብታቸውን በመነጠቃቸውና ህይወታቸውን እስከማጣት መድረሳቸው፣ ኢህአዴግ ለዘመናት ተዋዶና ተከባብሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ህዝብ ለመነጣጠል የሚጠቀምበት እኩይ ስትራቴጂ መሆኑን አናጣውም፡፡ በዚህ ተግባሩ በኢህአዴግ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ ባለስልጣናቱ ይዋል ይደር እንጂ በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት መጠየቃቸው የማይቀር ነው፡፡

በተለይም ባሳለፍነው ሳምንት ከመኖሪያ ቀያቸው "ወደ ክልላችሁ ሂዱ" ተብለው ሀብት ንብረታቸውን ጥለው ከተሸኙት ዜጎቻችን መሀከል 59 የሚሆኑት በመኪና አደጋ መሞታቸው በአካባቢው ነዋሪዎች ተረጋግጧል፡፡ መንግስት ሲያሳድዳቸው ህይወታቸውን ላጡ ዜጎች ልባዊ ሃዘናችንን እንገልፃለን፤ ለህይወት መጥፋቱ ግን መንግስት ሀላፊነቱን መውሰድ እንዳለበት እናምናለን፡፡ ያሟሟታቸውንም ሁኔታ የማጣራትና ለህዝብ የመግለፅ ግዴታውን እንዲወጣ ለማሳሰብ

እንወዳለን፡፡

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ህገመንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ መንግስት የጀመረውን የዘር ማፅዳት ዘመቻ የማስቆም ኃላፊነት አለበት፡፡ በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ከፍ ያለ ሸክም አለባቸው፡፡ እነዚህ ዜጎች የሚባረሩባቸው አካባቢዎች ያለው ህዝብም አጋርነቱን የማሳየት ግዴታ እንዳለበት እናምናለን፡፡


# ርዕዮት ዓለሙ ሁለተኛ ዲግሪዋን እንዳትማር ተደረገች

ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ የርቀት ትምህርት እንዳትማር መከልከሏን የዜና ምንጮቻችን አስታወቁ፡፡ የርዕዮት አለሙ ቤተሰቦችም የዜናውን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡

ለፍኖተ ነፃነት የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ርዕዮት እንደማንኛውም እስረኛ ሁለተኛ ዲግሪዋን ለመስራት ህንድ አገር በሚገኘው የሂንድራ ጋንዲ ናሽናል ኦፕን ዩኒቨርሲቲ አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅማ ብትመዘገብም ማረሚያ ቤቱ መጀመሪያ ከፈቀደ በኋላ ፖለቲካል ሳይንስ እንደምትማር ሲታወቅ ክልከላ ደርሶባታል ፡፡

የርዕዮት አለሙ እጮኛ ጋዜጠኛ ስለሺ ሀጎስ ስለጉዳዩ ጠይቀነው በሰጠን ምላሽ የርዕዮት ከዘጠኝ ወራት በፊት ትምህርቷን መቀጠል እንደምትፈልግ ለማረሚያ ቤቱ በማመልከቻ ጠይቃ እንደነበር አረጋግጧል፡፡ “ እኛ ለቱቶርና ለፈተና አንወስድሽም ግን ዩኒቨርሲቲው ፈታኝ ልኮ የሚፈትንሽ ከሆነና ቱቶር የሚሰጥሽ ከሆነ መማር ትችያለሽ የሚል ምላሽ በቃል ተሰጥቷታል፡፡ እኛም የዩኒቨርሲቲው ወኪል ከሆነው ቅ/ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር ጋር በመነጋገር ቃሊቲ ድረስ ፈታኝ ለሚላክበት ተጨማሪ አበል ለመክፈል ተስማምተን ምዝገባ አከናውነናል፡፡” በማለት የሚያስረዳው ስለሺ ሀጎስ ማረሚያ ቤቱ መስማማቱን ካረጋገጡ በኋላ ከሀያ ስድስት ሺብር በላይ ከፍለው ምዝገባውን እንዳከናወኑ ለፍኖተ ነፃነት ተናግሯል፡፡

በርዕዮት በተሰጠው ውክልና መሰረት የመማሪያ ሞጁሎች ይዞ ወደ ቃሊቲ



ያቀናው እጮኛዋ ስለሺ ሐጎስ እንደሚናገረው በማረሚያቤቱ የነበረው ሀላፊ የምትወስዳቸውም የፖለቲካ ሳይንስ ሞጁሎች ርዕስ ካነበበ በኋላ አናስገባልህም ተብሏል፡፡

ከክልከላው በፊት ሁለት የማይታወቁ ሰዎች የሂንድራ ጋንዲ ናሽናል ዩኒቨርሲቲ ወኪል ወደሆነው ቅ/ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በመሄድ “የርዕዮትን ሞጁል አምጡ” ማለታቸውን ጨምሮ የገለፀው ጋዜጠኛ ስለሺ በማረሚያ ቤቱ ክልከላ እንዳዘነ ለፍኖተ ነፃነት ተናግሯል፡፡
ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር እንዳለ በፍኖተ ነፃነት የተጠየቁት ወላጅ አባቷ ጠበቃ ዓለሙ ገቤቦ በሰጡት መልስ “ እውነት ነው፤ አንቺ እንድትማሪ አንፈቅድም ብለው ከልክለዋትል፡፡ በመሠረቱ አንድ በህግ ጥላ ስር ያለ እስረኛ ቀዳዳ እየተፈለገ መብቱን መንፈግ ተገቢ አይደለም፡፡ ምዝገባው ሲደረግና ሂደቶቹ ሲከናወኑ ፈቅዶ ትምህርቱ ሲጀመር መከልከል ተገቢ አይደለም፡፡ ችግሩን መፍታት የሚችል አካል ካለ አመልክተን ትምህርቷን የምትቀጥልበት መንገድ እንሞክራለን፡፡ ” ሲሉ መልሰዋል፡፡

ርዕዮት በቅርቡ ይቅርታ ጠይቃ እንድትፈታ በሽማግሌዎች ተጠይቃ ምንም ባልፈፀምኩት ወንጀል ይቅርታ አልጠይቅም የተፈረደብኝን ፍርድ እስር ቤት እጨርሳለሁ ብላ እንቢ በማለቷ ተደጋጋሚ አስተዳደራዊ በደል እየተፈጸመባት ይገኛል፡፡ በጡቷ ላይ በተፈጠረባት ህመም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፖታል ሪፈር ብትባልም መኪና የለም አጃቢ አልተገኘም በሚል ምክንያቶች ህክምናው መስተጓጎሉ ይታወሳል፡፡

**በውጭ ሀገር ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ለፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የህትመት መሳሪያ ማደራጃ ለመግዛት እንዲቻል ጥሪ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በጥሪው መሰረት በርካታ ወገኖቻችን ተግባራዊ ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው በወገኖቻችን እንድንኮራ አድርጎናል፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ወገኖቻችን በገንዘብ አላላኩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ በመጠየቃቸው ይህን ማብራሪያ አቅርበናል፡፡ ገንዘቡ የሚገባው በቀጥታ በፍኖተ ነጻነት አካውንት ነው፡፡**

1/በኦንላይን እርዳታ ለማድረግ ለምትፈልጉ በፔይፓል (pay pal secure payment)
እነዚህን ድህረ ገጾች ይጎብኙ

http://www.fnotenetsanet.com/
http://www.andinet.org/
http://www.andinetusa.org/

2/ በኤሌክትሮኒክስ ቀጥታ ለምታስተላልፉ

Andinet North America (Finote Netsanet News Paper)
Bank Name : Wells Fargo
ACC# 753-085-0978
Routing # 054-001-220

3/ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዘዣ (money order)

Andenet North America (Finote Netsanet News Paper)
P.O.Box 48355
Washington DC 20002
Tel. (202) 462-0556 Fax: (202) 462-0557

ማሳሰቢያ ፡ ገንዘቡን ገቢ ካደረጋችሁ በሁዋላ በሚቀጥለው ኢሜይል አድራሻ ብታሳውቁን ለስራችን ጥራት ይረዳናል፡፡
Email: info@andinetusa.org
ስለትብብራችሁ አስቀድመን ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡
በመላው አለም የምትገኙ ወገኖቻችንም ይህን መረጃ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በሰሜን አሜሪካ

# ኢህአዴግ አድርባይነትን ከማጥፋት ራሱን ማጥፋት ይቀለዋል

በዳዊት ሰለሞን

ዘጠነኛውን የኢህአዴግ ጉባዔ ተከትሎ ጎላና ረገጥ ባለ ድምጸት ሲነገሩ ካደመጥናቸው ቃላቶች መካከል አድርባይነት በእኔ እምነት ግምባር ቀደሙ ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ከዚህ ጉባዔ ቀደም ብሎ ህወሓት በመቀሌ ባደረገው ጉባኤ አድርባይነት የድርጅቱ ትልቅ ስጋት መሆኑ ስምምነት ተይዞበት ነበር፡፡ ምሬትና ቁጭት በሚነበብበት ስሜት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ‹‹አድርባይነትን መታገል እንደሚገባን አቋም ወስደናል፡፡ ድርጅቱን የሚያገለግሉ ሰዎች ስለ ሚያገኙት ደሞዝ ብቻ ማገልገል የለባቸውም፡፡›› በማለት አድርባይነትን መዋጋት አስፈላጊ ስለ መሆኑ አብራርተዋል፡፡

መቼም ኢህአዴግ ዘመቻ ይወዳል፡፡ የሚያደርጋቸውን ጠቅላላ ጉባኤዎች ተከትሎ በከፍተኛ ሹማምንቶቹ አማካኝነት የዘመቻ አጀንዳዎችን ይቀርጻል፡፡ ዘንድሮ ደግሞ አድርባይነትን እዋጋለሁ ብሎናል፡፡ የጉባኤው ተሳታፊዎችና እታች ያሉት ካድሬዎች ስለ አዲሱ የዘመቻ መፈክር እንጂ ስለ በፊቶቹ ብዙም ግድ ያላቸው አይመስሉም፡፡ ከዚህ በመነሳትም የአምናውና የአቻምናው ዘመቻ ምን ለውጥ እንዳመጣና በምን ደረጃ እንደሚገኝ የሚጠይቅ የለም፡፡ “ኪራይ ሰብሳቢነት”፣ “ሙስና”፣”ድህነት” ለመዋጋት ቆርጫለሁ በማለት ከዚህ ቀደም ዲስኩር ያሰማን ገዢው ፓርቲ ኪራይ ሰብሳቢዎችን፣ሙሰኞችን ከፊት ይልቅ በብዛት ማፍራት ችሏል፡፡ አሁን ደግሞ ሌላ አጀንዳ ተነስቷል ስሙም አድርባይነትን መዋጋት ተሰኝቷል፡፡

አድርባይነት መገለጫው ብዙ ቢሆንም ለመኖርና የግል ጥቅምን ለማሟላት ሲባል ያላመኑበትንና የማይከተሉትን የፖለቲካ አስተሳሰብ፣አቋምና መስመር የተቀበሉ በማስመሰል ሌሎችን መሸንገል ነው፡፡ ጥቅም ይገኝበታል ለተባለ ነገር ሁሉ ህሊናን በመሸጥ ለሆድ ማደር አድርባይነት ነው፡፡ አድርባይነትን በሀይማኖት መስመር ውስጥ በማስገባት ብንመነዝረው በውስጡ የምናገኛቸው ሰዎች ራሳቸውን ከጳጳሱ በላይ ክርስቲያኑ በማድረግ የሚወስዱ ናቸው፡፡

ኢህአዴግ ከ21 ዓመታት የስልጣን ላይ ቆይታው በኋላ ቀጣዮ አጀንዳው አድርባይነትን መዋጋት ስለመሆኑ ነግሮናል፡፡ አድርባይ የተሰኙት ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ አባላቶቹ ናቸው፡፡ ወ/ሮ አዜብም ሆኑ ድርጅቱ እነዚህን አድርባዮች በምን አይነት የፖለቲካ ላብራቶሪ መንጥረው ሊያወጧቸው እንደሚችሉ ዝርዝር መግለጫ ባይሰጡም ድርጅቱ በአድርባዮች የተወረረ ስለ መሆኑ የቀደምትና የአሁን ታሪኩን በመንተራስ መናገር ይቻላል፡፡ በምርጫ 1997 ኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ በአዲስ አበባና በዋና ዋና ከተሞች በዝረራ መሸነፉን ተከትሎ እስከታች እስከ ቀበሌ ድረስ በመውረድ ባደረገው ግምገማ የቀበሌ አመራሮች ጭምር ድምጻቸውን በወቅቱ ከፍተኛውን ድምጽ ላገኘው ለቅንጅት መስጠታቸውን አረጋግጧል፡፡

ሚያዚያ 28 እና 29 በአዲስ አበባ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ የተሳተፉ ብዛት ያላቸው ወጣቶች ለገዢው ፓርቲ ቀደም ብሎ በተደረገ የድጋፍ ሰልፍ መሳተፋቸውን የሚያሳይ በነጻ የታደላቸውን ቲ-ሸርት በማጥለቅ ‹‹ትናንት ለ ቲሸርት ዛሬ ለአንድነት›› በማለት በሁለቱ ቀናት ለሰልፍ የወጡበትን ምክንያት ማብራራታቸው አይዘነጋም፡፡ እዚህ ጋር መሰረታዊ ጥያቄ መነሳት ይገባዋል፡፡ ቲሸርት

> አድርባይ የተሰኙት ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ አባላቶቹ ናቸው፡፡ ወ/ሮ አዜብም ሆኑ ድርጅቱ እነዚህን አድርባዮች በምን አይነት የፖለቲካ ላብራቶሪ መንጥረው ሊያወጧቸው እንደሚችሉ ዝርዝር መግለጫ ባይሰጡም ድርጅቱ በአድርባዮች የተወረረ ስለ መሆኑ የቀደምትና የአሁን ታሪኩን በመንተራስ መናገር ይቻላል፡

በመስጠት ሰልፍ እንዲወጡ ያደረገው ማን ነው ሰዎችን በኢኮኖሚ ችግራቸው እየገባ መደለያ እያቀረበ ህሊናቸውን እየጣሉ እንዲከተሉት ያደረገ ድርጅት ዛሬ ድንገት ተነስቶ አድርባይነትን እዋጋለሁ ቢል ማን ያምነዋል?

### የዴሞክራሲ እጦትና የአድር ባይነት ቁርኝት

ኢህአዴግ እከተለዋለሁ የሚለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና መመሪያዎች ከላይ ወደታች ስለሚወርዱ የበታች ሹማምንትም የሚወርድላቸውን መመሪያ ሳይከልሱና ሳይበርዙ እንዲያወርዱ ያዛል፡፡ እናም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጭንቅላት የነበሩት መለስ ኒዮ ሊበራል፣ ጥገኝነት፣ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ በስብሰናል፣ ቦዘኔ .... ሲሉ የበታቾቻቸውም ምንም እንኳ ኒዮ ሊበራል ወይም ኪራይ ሰብሳቢነት የሚባሉ ፅንሰ ሀሳቦች ትርጉም ባይገባቸውም እነዚህኑ ቃላቶች በተነገሩበት የድምጽ ቶን መድገማቸው አይቀሬ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በፓርቲው ውስጥ የራሳቸውን ሃሳብ የሚያንሸራሽሩበት መድረክ ባለመኖሩና ይህንን ለማድረግ ከሞከሩም ምን እንደሚደርስባቸው ስለሚገነዘቡ የህሊና ጥያቄና ሙግትን በማፈን መስለው ያድራሉ፡፡

ኢህአዴግ ለውስጥ ዴሞክራሲ ባዕድ መሆኑን ለመገንዘብ ሩቅ ሳንሄድ በአባላቶቹ የተሞላውን ፓርላማ መመልከት ይበቃል፡፡ ፓርላማው ከአንድ ድርጅት ቁመት በላይ አገርን የሚመለከቱ አጀንዳዎች የሚነሱበትና ህጎች የሚጸድቁበት መድረክ ቢሆንም የመቀመጫ ወንበሮችን ያገኙ የተከበሩ ተወካዮች አንዱ ካድሬ የተናገረውን ‹‹እከሌ እንደተናገረው›› ከማለት ውጪ የተለየ ነገር ሲናገሩ ተደምጠው አያውቁም፡፡ ይህም ድርጅቱ አድርባይነትን ተሸክሞ ለመቆየቱ አይነተኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ ኢህአዴግ አድርባይነትን መዋጋት ድርጅቱን በገዛ ራሱ እንዲጠፋ የሚያደርገው በመሆኑ ‹‹ አድር ባይነትን እዋጋለሁ›› ማለቱ ከዲስኩር አይዘልም፡፡

በነገራችን ላይ ኢህአዴግ አድርባዮችን ከምር የሚዋጋ ከሆነ የፎረሞች፣ የሊጎች፣ የሴቶች ማህበራት፣ የአርቲስቶች ማህበርና ሌሎችም ምን ሊውጣቸው ነው? መልሱ ናፈቀኝ፡፡

# ከቤንሻንጉል አማርኛ ተናጋሪ ዜጎችን በግፍ የማፈናቀሉ ተጠናክሮ ቀጥሏል

## -ጥቃቱ ህፃናትና አረጋውያን ላይም እየደረሰ ነው

አማርኛ ተናጋሪውን ከየቦታው የማፈናቀሉ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን የመረጃ ምንጮቻችን አስታወቁ፡፡ የፍኖተ ነፃነት ምንጮች እንደሚሉት በዚህ ሳምንት ውስጥ ብቻ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማይ ዞን ያሶ ወረዳ 25 ሺህ አማርኛ ተናጋሪዎች እየተደበደቡ በጭነት መኪና ተጭነው ከመኖሪያቸው ተባረዋል፡፡ የአካባቢው የዓይን ምስክሮችም ተጧሪ አረጋዊያንና ህፃናት "ውሃ፣ አምባሻ እያሉ በየመንገዱ ሲለምኑ ያለርህራሄ እየደበደቧቸው ወስደዋቸዋል፡፡" ሲሉ በቅሬታ ያስረዱሉ፡፡

ፍኖተ ነፃነት ያነጋገረቻቸው የዓይን ምስሮች እንደሚሉት መንታ የተገላገለች እመጫት ሳትቀር አስር ቀን ሳይሞላት በጭነት መኪና ላይ ወርውረዋት አከባቢውን ለቃ እንድትሄድ ተደርጓል፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ለመረዳት እንደቻለው አብዛኞቹ ተፈናቃዮች ከ96 ዓ.ም ጀምሮ በባዶ መሬት ላይ ሠፍረው አካባቢውን ያለሙ የነበሩ ናቸው፡፡ የዘሩትን እህል ሳይሰበስቡና ንብረታቸውን ሳይዙ እየተባረሩ የሚገኙት እነዚህ የአማርኛ ተናጋሪ ዜጎች የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችም እየደረሱባቸው እንደሚገኝ ፍኖተ ነፃነት ከአይን እማኞች ለማረጋገጥ ችላለች፡፡ ምንጮቻችን አክለውም "ሰው መሆን እስከሚያስጠላ ድረስ በጭካኔ እየደበደቡ መሬት ለመሬት እየጎተቱ መኪና ላይ ይወረውሯቸዋል፡፡ በአካባቢው ኦሮሚኛ እና ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች በተመሳሳይ ጊዜና ከዚያ ወዲህ በቅርብ ጊዜ ሠፍረው የሚኖሩ አሉ፡፡ እነሱን የሚነካቸውና የሚጠይቃቸው የለም፡፡" በማለት አማርኛ ተናጋሪዎች ላይ ያነጣጠረ ዘር የማፅዳት ዘመቻ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ፍኖተ ነፃነት ያነጋገረቻቸው በአካባቢው በንግድ ስራ የተሰማሩ ግለሰብ እንደሚናገሩት አማርኛ ተናጋሪዎቹን ከስፍራው ለማፈናቀል ከሚሰጡት ምክንያት አንዱ "ከዚህ በፊት በክልላችሁ በነበራችሁበት ቦታ የማዳበሪያ ዕዳ አለባቸው" የሚል ነው፡፡ ግለሰቡ አክለውም "ዕዳ ካለባቸው ባሉበት በህግ መጠየቅ እየተቻለ ሁሉንም ወንጀለኞች ናቸው እየተባለ መደብደብና ማባረር ወንጀል ነው፡፡" ብለዋል፡፡ አያይዘውም ብአዴን በአማራ ህዝብ ስም ሥልጣን ላይ ተቀምጦ በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈጸመውን እያየ እንዳላየ ዝም ብሎአል፡፡ አቤቱታ እየቀረበላቸው አንድም ነገር አላሉም፡፡ ብአዴን የአማራ ህዝብ ወኪል አለመሆኑን ሙሉ በሙሉ ያረጋገጠበት ወቅት ላይ ደርሷል፡፡" ሲሉ እጅግ አዝነው ተናግረዋል፡፡
ጉዳዩን እያስፈጸሙ ናቸው የተባሉትን የወረዳውን አስተዳዳሪ አቶ ታደሰ ሻምበልን በስልክ አግኝተናቸው ነበር፡፡ እራሳችንን አስተዋውቀን ጥያቄያችንን ልንጀምር ስንል አቶ ታደሰ ስልካቸውን ጆሮአችን ላይ በመዝጋታቸው ዜናው ሚዛናዊ ለማድረግ አልቻልንም፡፡

በዚህ ሳምንት ከወረዳው ተባረው በመጓጓዝ ላይ የነበሩ ዜጎችን ጭኖ የነበረው አንዱ መኪና ተገልብጦ 59 ሰዎች ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል፡፡ ህይወታቸው ካለፈው ውስጥ አብዛኞቹ ህጻናት፣ሴቶችና አረጋውያን መሆናቸውን በስፍራው የተገኙ የዓይን ምስክሮች ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል፡፡

# በመላው አገሪቱ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየተባባሰ መቀጠሉ ተገለፀ

በመላው አገሪቱ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተባብሶ መቀጠሉ ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለፀው 22ኛው የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ /ሰመጉ/ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ነው፡፡ ከመላው አገሪቱ የመጡ ጉባኤተኞች በስብሰባው ላይ እንዳስታወቁት በጎንደር ፣በአርባምንጭ፣በአዋሳ፣ በባህርዳር ፣በድሬዳዋ፣በሐረር፣በጂጂጋ እና በተለያዩ ኦሮሚያ ክልሎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተባብሶ መቀጠሉን አስታውቀዋል፡፡

ባለፈው እሁድ በድርጅቱ ዋናው ጽ/ቤት በተደረገው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የመክፈቻውን ንግግር ያደረጉት የሰመጉ ቦርድ ሰብሳቢ ወ/ሮ እልፍነሽ ደምሴ ናቸው፡፤ ዓመታዊ የሥራ ሪፖርት በሰመጉ ዳሬክተር በአቶ እንዳልካቸው ሞላ ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ሲሆን ለሚቀጥው ዓመት ሥራ ላይ የሚውል እቅድ ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በመጨረሻም ሰመጉን የሚቀጥለው 3 ዓመታት የሚመሩ አምስት ሥራ አስፈጻሚ ተመርጠው አቶ ይስሃቅ ገ/ማርያም የሰመጉ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል፡፡
በሌላ በኩል ሰመጉ ሰሞኑን 124ኛውን ልዩ መግለጫ አውጥቷል፡፡ መግለጫው እንደሚዘረዝረው በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ የመሰብሰብ ነፃነት አለመኖሩን፣የሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ መብት ጥሰት እየተፈፀመ መሆኑን፣ ህገወጥ እስር እንደሚደረግ በመዘረርዝር አስቀምጧል፡፡ የተቋማት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ክልከላ መደረጉን አሳይቷል፡፡

# በሜክሲኮ ቤቶች በመፍረሳቸው ከ500 ሰው በላይ ከሥራ ተፈናቅሏል

አዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ ቡናና ሻይ ህንጻ ፊት ለፊት በሚገኙ ንግድ ቤቶች በመፍረሳቸው ከ500 በላይ ዜጎች ከሥራ መፈናቀላቸውን በአካባቢው የተዘዋወረው የፍኖተ ነፃነት ሪፖርተር ዘገበ፡፡
ከሥራቸው የተፈናቀሉትንና የአካባቢውን ነዋሪዎች ያነጋገረው ሪፖርተራችን እንደዘገበው በስፍራው ቤት ፈርሶባቸው ሥፍራ በመሆኑ ቁጥራቸው ከ35 በላይ የሚሆኑ ሱቆች ነበሩበት፡፡ በቦታው ከ500 ሰው በላይ ሠራተኞችም ነበሩ፡፡ ሁላችንም ከሥራ በመበተናችን ለችግር ተጋልጠናል፡፡" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተውታል፡፡
አስተያየት ሰጪዎቹ እንዳሉት "ቦታውን በአስቸኳይ ልቀቁ ብለው ስላአጣደፉን ሱቅ ውስጥ ያሉትን ሸቀጦች የምናደርግበት ቦታ በማጣታችን ከገዛንበት በታች ለመሸጥ አልሰጡንም ፡፡አሁን ቤቶቹ ፈርሰው ባዶ መሬት የተቀመጠበትን ጊዜ ቢሰጡን ኖሮ እንኳን ቢያንስ እቃችንን ባመጣንበት ዋጋ የመሸጥ ዕድል እናገኝ ነበር፡፡ እነሱ ግን በሁለት ቀንና በ3 ቀን ውስጥ ታሪክ የሚሠሩ ይመስል አዋክበውን በርካሽ አሸጡን፤ ምትክ የሥራ ቦታ ባማግኘታችን እቃችንን በኪሳር ሸጠን ተቀምጠናል፡፡"ሲሉ አማረዋል፡፡

# “የኢህአዴግ እብሪትና ትዕቢት አገርንና ህዝብን የሚያጠፋ ነው”

## አቶ ግርማ በቀለ 33ቱ ፓርቲዎች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ

**የዛሬው እንግዳችን አቶ ግርማ በቀለ ይባላሉ ፡፡ አቶ ግርማ በቀለ በቅርቡ የትብብር ሠነድ የተፈራረሙት 33ቱ ፓርቲዎች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ እና የኦሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ህብረት /ኦህዴህ/የተባለ ፓርቲ ሊቀመንበር ናቸው፡፡**



**ፍኖተ ነፃነት፡- ፔቲሽን ፈራሚ ፓርቲዎች አሁን በምን እንቅስቃሴ ላይ ናቸው?**

አቶ ግርማ፡- የፔቲሽን ፊርማው ወደ ትብብር ሠነድ ከተሸጋገረ በኃላ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። የቀጣይ 6 ወራት ተግባር እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ትብብሩን ለሚቀጥለው 6 ወራት የሚመራ ቋሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ለማስመረጥ በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ እስከ አሁን ድረስ ስንቀሳቀስ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም፡ ፡ ከውስጥም ከውጪም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመቋቋም እዚህ ደርሰናል፡፡ አሁን የደረስንበት ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ነው።

**ፍኖተ ነፃነት፡- ትብብሩ ስስ ነው፤ ትንሽ ቆይተው አለመግባባት ይፈጥራሉ፤ሁሉም አብረው አይዘልቁም የሚሉ ወገኖች አሉና እርስዎ ምን ይላሉ?**

አቶ ግርማ፡-የማራቶን ውድድር አብረው የጀመሩ ሁሉ አይጨርሱም፡፡ እጅግ ውስብስብና ፈታኝ በሆነ ሠላማዊ ትግል አብሮ የጀመረ ሁሉ አብሮ ይጨርሰሳል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ትግሉ እየጠራና እየገፋ በሄደ ቁጥር እየተራገፈና እየተንጠባጠበ ሊቀር ይችላል። እስከ አሁን በይፋ ለቅቁአለሁ ብሎ በይፋ መግለጫ የሰጠ ፓርቲ ባይኖርም በተግባር ግን እስአሁን አምስት ድርጅቶች ግንኙነታቸውን አቋርጠዋል፡፡ ነገ ሌላ ሊቀጥል ይችላል፡፡ 15 ወይም 20 ፓርቲ ነጥሮ ቢወጣ አያስገርምም ቁምነገሩ ቁጥሩ ላይ አይደለም ዋናው ቁም ነገር ፓርቲዎቹ ሕዝብና አገር የሚፈልገውን ተግባር እያከናወኑ ናቸው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ከህዝብ የሚጠበቀው አመራሩን በቅርብ መከታተለና መቆጣጠር ነው፡፡ ድክመቶችንና ችግሮቹን ብቻ እየነቀሱ በማውጣት መተቸት ሳይሆን እኔንም ያገባኛል ብሎ ከትግሉ መቀሳቀል ያስፈልጋል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- ህዝብ ዘንድ እንዴት እንደርሳለን? ህዝቡንስ እንዴት ወደ ትግሉ እናስገባለን ብላችሁ ታስባላችሁ?**

አቶ ግርማ፡- ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ከህዝብ እንዳይገናኙ የማያደርገው ጥረት የለም፡ ፡ ህገመንግስቱን ጥሶ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት ፣ሠላማዊ ሠልፍ ማድረግ እየከለከለ ነው፡፡ እኛ ግን መብታችንን ተጠቅመን ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡ ዛሬ ሙሉ ለሙሉ በሚባልበት ሁኔታ የሚዲያ አፈና ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ያሉትን ሚዲያዎች ሁሉ እንጠቀማለን፡፡ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎችን ድህረ ገጾችን በመጠቀም ዓላማችንን እናስተዋውቃለን፡፡ የየፓርቲዎችን መዋቅር እንጠቀምበታን፡፡ የሲቪክስ ማህበራትን መዋቅርም እንዲሁም የመንግስት ሚዲያዎችን እንጠቀማለን ፡፡ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ እንጠቀማለን፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- የወቅቱን የአገሪቱን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ይገልጹታል?**

አቶ ግርማ፡- እንደ 33ቱ ፓርቲዎች በጋራ ገምግመን የደረስንበት ድምዳሜ የለም።
ጥያቄህን እንደ ግል የማምንበትን ልመልስልህ፡ ፡ አገራችን ከፍተኛ ችግር ውስጥ የወደቀችበት ጊዜው ነው፡፡ አገራችን ዛሬ በማንኪያ የተያዘች፤ ከሥሯ ድንጋይ የሚጠብቃት እንቁላል ሆናለች፡፡ አገራችን በዚያ ድንጋይ ላይ ወድቃ እንዳትከሰከስ ሁላችንም እጃችንን ዘርግተን እንቁላሏን ለማዳን መጠባበቅ አለብን። የኢህአዴግ እብሪትና ትዕቢት አገርንና ህዝብን የሚያጠፋ ነው። የሀገራችን ሁኔታ አሁን ካለበት ወደ ባሰ ደረጃ እየተጓዘ ነው፡ ፡ ህዝብን እያገለለ ሚዲያን እያፈነ የተለየ ሐሳብ ያለውን ሰው እያጠፋ መጓዝ ይፈልጋል፡፡ ይህ ጉዞ እጅግ አደገኛ ነው፡፡ ህዝቡ ተረድቶታል፡፡ እባካችሁ ተባበሩና ምሩን ሲል ቆይቷል፡፡ እኛም ተባብረናል፡ ፡ ከእንግዲህ በቁርጠኝነት አገር የማዳን ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

**ፍኖተ ነፃነት፡- አንዳንድ ወገኖች መንግስት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ነው፣ የተወሰነን ብሔር ለማጥቃት የተነጣጠረ ዘመቻ ጀምሯል ይላሉ፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?**

አቶ ግርማ፡- ከጅምሩ የዚህን መንግስት አነሳስ ስንመለከት ገና በረሃ እያለ ዋና ጠላቶች ናቸው ብሎ የፈረጃቸው አሉ፡፡
ከብሔረሰብ አማራን ከሃይማት ኦርቶዶክስን በጠላትነት ፈርጇል፡፡ የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ ለመመለስ እነዚህን ሁለቱን ማጥፋት ያስፈልጋል ብሎ አቀደ፡፡ ሁለቱም የአገርና የህዝብ ጠላቶች ናቸው በማለት እንደዓላማ ወይንም እንደ አቅጣጫ አስቀመጠ። ከተለያየ ቦታ የተገኘ መረጃ የሚያለክተውም ይህንኑ ነው፡፡

ገና ትግራይ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ከየቤተክርስቲያኑ ካህናትን በማባረር ቤተክርስቲያኖችን በካድሬ ቄሶች እንዲመሩና እንዲተዳደር አድርጓል፡፡ የመንግስት ሥልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ በአማራውና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ሲፈፀም የነበረውን ሁሉ የምናውቀው ነው፡፡ ይህን መናገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል፡፡

ሰሞኑን በአማራው ህዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለውንም ይታወቃል፡፡ በቅርቡ ደግሞ የሃይማኖት ት/ቤታችንን ራሳችንን እናስተዳድር የሃይማኖት መሪዎቻችን እኛን አይወክሉም፤ መጅሊሳችንን ራሳችን እንሰይም፤ አህባሽ የተባለ ባዕድ አስተምሮ ከውጭ አምጥታችሁ አትጫኑብን፤ ብለው በሠላማዊ መንገድ የጠየቁ የተከበሩ የሙስሊሙ የሃይማት አባቶች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ድርጊት እየተመለከትን ነው፡፡ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ለሠላማዊ ትግል አስተማሪ በሆነና በሠለጠነ መንገድ ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡

መማር ለሚችል ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ትግስትና ሠላማዊ ተቃውሞን ተምሯል፡፡ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ህዝብን በሃይማኖት ከፋፍሎ ለማፋጀትና ዕድሜውን ለማራዘም ያደረገው ጥረት ከሽፎበታል።

የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት የጠየቁት ጥያቄ መንግስት በሃይማኖታቸው ጣልቃ እንዳይገባባቸው ነው፡፡ ስለዚህ መፍትሔው ከእንግዲህ ሙስሊሙ ክርስቲያኑ መላው የአገሪቱ ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ይህን ሥርዓ ለመቀየር በቁርጠኝነት በጋራ መታገል ነው፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

# ለዜጎች መሞት፣ መፈናቀልና መሰደድ ተጠያቂው መንግስት ነው!!!

# ወንጀለኞች በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን

## ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ(አንድነት) የተሰጠ መግለጫ

በተደጋጋሚ ፓርቲያችን እንደሚገልፀው አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የሚከተለው ቋንቋን መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝምና የስርዓቱ አራማጆች ካላቸው የስልጣን እድሜን የማራዘም ጉጉት ተደማምረው ለሃገራችን እንዲሁም ተቻችሎ፣ ተዋልዶ፣ ተዛምዶና ተዋድዶ ለዘመናት ይኖር ለነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅና አስፈሪ አደጋ ወደ መሆን እንደደረሱ በግላጭ እየታየ ነው፡፡

ያ ለዘመናት አብሮን የቆየው በጋራ የመኖር ዕሴት እየተደመሰሰ በምትኩ የሚያጋጩ ስልቶች እየተፈጠሩና እየተተገበሩ ወደ ሰቆቃ ተለውጠው ይገኛሉ፡፡ የዜጎች ሰዋዊና ህጋዊ መብት እየተጣሰም ነው፡፡ በኢትዮጵያችን ውስጥ አብሮ የመኖር፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋወርና በፈለጉት ቦታ ሃብት የማፍራት ህልውና እያከተመ መጥቷል፡፡ ለዚህ ክፉ ድርጊት ተጠያቂ የሚሆነው ደግሞ የዜጎችን መዘዋወር መብትና ሃብት የማፍራት መብት ማረጋገጥ የተሳነው መንግስትና መንግስት ብቻ ነው፡፡

የከዚህ በፊቱን የማፈናቀል ግፍ ትተን በቅርቡ እንኳ በጉረፈርዳና በሌሎች አካባቢዎች በቀጥታ በክልሉ ባለስልጣናት በተፃፈ ደብዳቤ ይሄ ሀገራችሁ አይደለም ተብለው፣ ሃብትና ንብረታቸው ተዘርፎ፣ የወለዱ አራሶች እንኳን የማገገሚያ ጊዜ ሳይሰጣቸው ደማቸውን እያዘሩ ሲባረሩ ከመንግስት የተሰጠው ምላሽ ‹‹ሞፈር ዘመቶች ናቸው (ማረሻውን ብቻ ተሸክሞ ወደ ሌላ ሀገር የሚሰደድ ለማለት ይመስለናል)›› የሚል ነበር፡፡ ይሄም ቢሆን የማንኛውም ዜጋ መብት ነው፡፡ መንግስት እነዚህ ዜጎች ‹‹ሃገራችን የት ነው?›› በማለት ለሚያነሱት ጥያቄ መልስ የለውም፡፡

ገዥው ፓርቲ ሃላፊነትን መዘንጋትንና ስህተትን በማረም ፈንታ አፋፍሞ በመቀጠል ዜጎች ሃብትና ንብረታቸው እየተዘረፈ መባረራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይህም በጋምቤላና ቤኒሻንጉል በከፋ መልኩ ቀጥሏል፡፡ በተለይ ከቤኒሻንጉል ክልል የአማራ ተወላጅ የሆኑትን ዜጎች የዘመናችን ሹመኞች ከኢ-ሰብዓዊነት ባፈነገጠ መልኩ ከእቃ ለሚሰጥ ክብር ባነሰ ሁኔታ ንብረታቸውን ሳይሰበስቡ በጅምላ እየተጫኑ መጣላቸውን ቀጥለዋል፡፡ በርካታ ህፃናትም የዚህ ግፍ ሰለባ ሆነዋል፤ እየታፈኑ የሚሞቱትም ቁጥራቸው በርካታ ነው፤ በጣም የሚያሳቅቀው ደግሞ የዚህ ግፍ ሰለባ የሆኑት 59 ሰዎች ሞት ጉዳይ ነው፡፡ ካላግባብ በጭካኔ ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት፣ ከወለዱበትና ከከበዱበት ስፍራ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ በአንድ መኪና እየታጨቁ እንዲወጡ በማድረግ ገደል ውስጥ ገብተው እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ዜጎችን ህይወት እንዲቀጠፍ ያደረገውም በቸልታ እየገዛ ያለው የኢህአዴግ መንግስት ነው፡ ፡ መንግስት በነዚህ ዜጎች ላይ ለደረሰው ኢ- ሰብዓዊ ድርጊትና ህይወት ማጣት ተጠያቂ ነው በማለት ፓርቲያችን ያምናል፡፡

ፓርቲያችን አንድነትም ጥያቄ ያነሳል፡፡ ለውጭ ዜጎች እንዲበለፅጉበት በትንሽ ሳንቲም፤ ግልፅነት በጎደለውና በሙስና በተተበተበ አሰራር ለቻይና ኩባንያዎች፣ ለህንድ ኩባንያዎች፣ ለሳውዲ አረቢያ ኩባንያዎች ወዘተ ለዜጎቻቸው ቀለብ እንዲያመርቱበት በገመድ እየተለካ የሚሰጠው የአዲስ አበባን ስፋት አምስት ጊዜ የሚበልጥ መሬት እንዴት ለዜጎቹ ይነፈጋል? ለምንስ ኢትዮጵያውያን ተዘዋውረው በኩርማን መሬት ላይ ሃብት የማፍራት መብታቸውን ተነፈጉ? ይህንን ኢሰብአዊነት ዓለማቀፉ ማህበረሰብ፣ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲያውቁት እንፈልጋለን፡፡ ኢህአዴግንንና በእሱ የሚመራውን መንግስት ታሪክና ሕዝብ ይፋረደዋል፡፡ ይህንንም በደል እያዩና እየሰሙ ዝም ማለት የወንጀሉ ተባባሪ መሆን ማለት ነው፡፡ ዛሬውኑ ተቃውሞአችንን፣ ጩኸታችንን እናሰማ፤ በደል ሰቆቃ በቃ እንላለን፡፡ በአቋማችንም፡-

1.ለዚህ ሁሉ አገራዊ ቀውስ ተጠያቂው መንግስት መሆኑን
2.ዜጎች እንዲሞቱ፣ እንዲጎሳቆሉና እንዲሰደዱ ያደረጉ ወንጀለኞች በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ
3.የሴቶችና ህፃናት መብት እንዲከበር
4.ማፈናቀሉ አሁኑኑ እንዲቆም
5.ተጎጅዎችም ካሳ እንዲከፈላቸው እንጠይቃለን፡፡

# አንድነት ፓርቲ በዜጎች ሞት፣ መፈናቀልና መባረር የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልፃል!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
መጋቢት 20 ቀን 2005 ዓ.ም

# “እኛስ ሀገራችን የት ነው?”


ወጣት እየሩሳሌም
የጉለሌ ክ/ከተማ ስራ አስፈፃሚ


ወጣት ብርሀኑ ተክለያሬድ
የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር
ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር


ወጣት ጋሻው መርሻ
የጉለሌ ክ/ከተማ ስራ አስፈፃሚ

የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር የሆነው ወጣት ሀብታሙ አያሌው በተደጋጋሚ በማህበሩ አባላት ላይ ስለሚደርሱ የህግ ጥሰቶች በተለያዩ ብዙሀን መገናኛዎች ላይ መግለጫዎችን ሰጥቷል፡፡ በቅርቡ የተደረገውን ፀረፋሺስት የተቃውሞ ሰልፍ ተከትሎ በርካታ የማህበራቸው አባላት መታሰራቸውን፣ መደብደባቸውንና ከስራቸው መባረራቸውን ለፍኖተ ነፃነት ይናገራል፡፡ “ጣሊያኖች ኢትዮጵያውያንን በግፍ መግደል ያስሸልማል፤ ጀግና ያሰኛል ብለው ለግራዚያኒ ሀውልት መስራታቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ ያላቸውን ንቀት ያሳያል” የሚለው ሀብታሙ አያሌው ፋሺስትን ለመቃወም የወጡ ወጣቶችን መንግስት ማሰሩና ማንገላታቱ አሳዝኖታል፡፡ “እኛ ለሀገራቸው የሞቱት አርበኞች የልጅ ልጆች ነን፤ የኢትዮጵያ ልዕልና መደፈር የለበትም፣ ጀግኖች አባቶቻችን የከፈሉት መስዋዕትነት ሊረክስ አይገባም ብለንነው ሰልፉን ያስተባበርነው” በማለት የሰልፉን አላማ ያስረዳል፡፡

በሰልፉ ላይ ከተያዙት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን መካከል የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አባላት ላይ ከበድ ያለ ምርመራ ተካሂዶባቸዋል የሚለው ወጣት ሀብታሙ “ከታሳሪዎች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አባላትና አመራሮች ናቸው፡፡” በማለት ብራራል፡፡ የኢህአዴግን ከአንባገነን በላይ መሆን የተመለከተው ወጣት ሀብታሙ በማህበሩ ውስጥ ከሚያካሂደው ተሳትፎ በተጨማሪ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ ወስኗል፡፡ ሀብታሙ በርካታ ፓርቲዎችን ተመልክቶ መዳረሻውን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሆኗል፡፡

ወጣት ብርሀኑ ተክለያርድ ይባላል፤ የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ነው፡፡ መጋቢት 8 የኢትዮጵያ ክብር ተቆርቋሪ የግል ተነሳሽ ኮሚቴና የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር በዋነኝነት ላዘጋጁት ፀረፋሺስት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ እያለ በፖሊስ ተይዞ ለሁለት ቀናት ታስሯል፡፡ ያሬድ በምን አይነት ሁኔታ እንደተያዘ ሲያስረዳም “መጋቢት 8 ለሚካሄደው ሰልፍ መጋቢት 7 ህዝቡ በሰልፉ ላይ እንዲገኝ በመኪና ቅስቀሳ እያካሄድ ነበር፡ ፡ ከሰማያዊ ፓርቲ ጽ/ቤት በመነሳት አራት ኪሎ፣ስድስት ኪሎና ሽሮሜዳ አካባቢ ቀስቅሰን ፒያሳ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ስንደርስ ፖሊሶች ተከታትለው አስቆሙን ህገወጥ ቅስቀሳ እያደረጋችሁ ነው ብለውን ወደ ጃንሜዳ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱን” በማለት ፖሊስ ጣቢያ ከመድረሱ በፊት የነበረውን ሁኔታ ያስቃኘናል፡፡

ፖሊስ ጣቢያ እንደደረሱ ያጋጠማቸውን ሲያስረዳም “እዛ ስንደርስ ኮማንደር ኃይሉ ሀለፎም የሚባል ሰው አገኘንና ህገወጥ ቅስቀሳ እያደረግን እንደሆነና ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት እንዳለን በመንገር፣ በማስፈራራት ሁላችንም ስልካችንን እንድንቀማ አደረገን፡፡ ከዛም ስንበትነው የነበረው ወረቀት ተቆጥሮ በእያንዳንዱ ላይ እንድንፈርም የመጠየቅና አድራሻ ስንሰጥ ደግሞ በግድ ብሔር እንድንናገር የማስፈራራት፣የማስገደድና የማዋከብ ሁኔታ ነበር፡፡ ቅዳሜ አስር የሚሆኑ መርማሪዎች ነን የሚሉ ሰዎች እየተፈራረቁ ብሄራችንን እንድንናገር የማስፈራራትና የማዋከብ ድርጊት ሲፈፅሙብን ነበር፡፡” በማለት ብሔር ላይ ያተከረ ምርመራ እንደተደረገባቸው ይጠቅሳል፡፡

> **የኢህአዴግን ከአንባገነን በላይ መሆን የተመለከተው ወጣት ሀብታሙ በማህበሩ ውስጥ ከሚያካሂደው ተሳትፎ በተጨማሪ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ ወስኗል፡፡ ሀብታሙ በርካታ ፓርቲዎችን ተመልክቶ መዳረሻውን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሆኗል፡፡**

ቀጠል አድርጎም "በዕለቱ ምግብ እንዳይገባልንና ከቤተሰብ እንዳንገናኝ ተደርጎ ከለሊቱ አምስት ሰዓት ሲሆን ሶስት ሰዎች ጃን ሜዳ ፖሊስ ጣቢያ፣ ሁለት ሰዎች ራስ ደስታ ፖሊስ ጣቢያ እንዲሁም ሌሎች ሶስት ሰዎች አራዳ ማዘዣ ጣቢያ እንድናድር ነው የተደረገው፡፡ በተለይ አራዳ ማዘዣ የነበርነው ሶስት ሰዎች ማለትም ዮዲት አገዘ የምትባል የማህበራችን አባል በረንዳ ላይ እንድታድር አደረጓት፡፡ ሁለታችን ደግሞ አንድ ባዶ ክፍል ውስጥ ባዶ ሲሚንቶ ላይ እንድንተኛ ተደርገናል፡፡" በማለት የደረሰባቸውን ግፍ ይዘረዝራል፡፡

ያሬድ በታሰሩበት ወቅት አካላዊና ስነልቦናዊ ጥቃት ደርሶባቸው እንደነበርም ይናገራል "እሁድ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በጣቢያው ያሉ የትራፊክ ቢሮዎች እንዲለቀቁ ተደርጎ ደህንነቶች ሊመረምሩን ወሰዱን፡፡ መጀመሪያ የገባሁት እኔ ነኝ፤ የመረመረኝ ሳምሶን የሚባል የአራዳ ክ/ከተማ ደህንነት ነው፡፡ በጣም አፀያፊ ስድቦችን ይሰድበኝ ነበር፡፡ ወደ ክፍሉ ያስገባቺኝ የዕለት ሁኔታ መዝጋቢ ልክ እንደገባሁ ገፈተረቺኝ፣ እሷ ስትገፈትረኝ መርማሪውም ኩላሊቴን ረገጠኝ አቅም አጥቼ ቁጭ አልኩ፡፡ ደህንነቱ የጠየቀኝ የመጀመሪያ ጥያቄ ብሔሬን እንድንናገር ነበር፤ ብሔር አልናገርም ስል በሩን ቆልፈው ድብደባ ጀመሩ፡፡ ከዛም ሴቷን አስወጣትና ድብደባውን ቀጠሉ፡፡ በር ባንኳኳም የሚደርስልኝ አላገኘሁም፡፡" በማለት የደረሰበትን ጥቃት ያስታውሳል፡፡

ወጣት ያሬድ በድብደባው ወቅት ከአንድነት ፓርቲ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምንድነው? ከሰማያዊ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምንድነው? እናንተ የአሸባሪ ድርጅቶች ተላላኪ ናችሁ፡፡ እንዳሉት ያስታውሳል፡፡ "የፌስቡክ የይለፍ ቃልህን(password) ካላመጣህ" በሚል ከፍተኛ ድብደባ የደረሰበት ያሬድ ይህ ኢሰብአዊ ምርመራ ምን ያክል ጊዜ እንደወሰደ ሲገልፅ "በአጠቃላይ ለሁለት ሰዓት እየተደበደብኩ ቃሌን እንድሰጥ ተደርጌያለሁ፡፡ በተጨማሪም ስለቤተሰቤ ይነግሩኝ ነበር እከሌ የሚባል ወንድም አለህ፣ እከሊት የምትባል እህት አለችህ ይሉኝ ነበር፡፡ ጌታነህ የሚባል የሰማያዊ ፓርቲ አመራርም ድብደባ ደርሶበት ልብሱ በደም ተጨማልቆ ሲወጣ አይቻለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በግዳጅ ፎቶ እንድንነሳና ቪዲዮ እንድንቀረፅ ተደርጓል፡፡" ይላል፡፡

ሌላዋ የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አባል እየሩሳሌም ትባላለች የጉለሌ ክ/ከተማ ስራ አስፈፃሚ ነች፤ እሷም መጋቢት 8 በተካሄደው ፀረፋሺስት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በመሳተፏ ለእስር ተዳርጋለች፡፡ እየሩሳሌም በእለቱ የነበረውን ሁኔታ እንደሚከተለው ታስታውሰናለች "መጋቢት 8 ጠዋት ሶስት ሰዓት ላይ ስድስት ኪሎ ሰማዕታት ሀውልት አካባቢ ቀድመን የደረስን የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አባላት፣ በማህበራችን የተዘጋጀውን ቲሸርት ለብሰን መሰባሰብ ጀመርን፡፡ ወዲያው ኮማንደር ኃይሉ ሀለፎም የሚባል ግለሰብ(ሲቪል ለብሶ) ተበተኑ አለን" ትላለች፡፡ ኮማንደሩ ወጣቶቹ እንዲበተኑ ያዘዘበት ምክንያት "ፍቃድ የላችሁም፤ ህገወጥ ናችሁ" የሚል ነበር፡፡ እነእየሩሳሌም ግን "ማሳወቅ እንጂ ማስፈቀድ አይጠበቅብንም" የሚል ምላሽ ቢሰጡም ፖሊሶች መጥተው በሀይል በትነዋቸዋል፡፡ "ሰልፉ ከተበተነ በኋላ ወደ ሰማያዊ ፓርቲጽ/ቤት መሄድ እንደጀመርን አንበሳ ግቢ ስንደርስ ቲሸርታችሁን አውልቁ፤ ቲሸርታችሁ ህገወጥ ነው በማለት ፖሊሶች አዋከቡን" የምትለው የባለራዕይ ማህበር አባል፣ በፌስታል የያዘቻቸውን ቲሸርቶች ፖሊሶች በሀይል ሊነጥቋት መሞከራቸውን ታስረዳለች፡፡ "ቲሸርቱን አምጪ ብለው በዱላ ደበደቡኝ ከዛም በሀይል መኪና ውስጥ ጫኑኝ፡፡ መኪና ውስጥ ካስገቡን በኋላ ወንድ ፖሊሶች እኔንና አብረውኝ የነበሩ ሴቶችን በዱላ፣በጥፊና በቦክስ ተቀባበሉን" የምትለው ወጣት እየሩሳሌም ከሷ ጋር የተያዙት ሰልፈኞች አራዳ ፖሊስ መምሪያ እንዲገቡ መደረጉን ትናገራለች፡፡

ፖሊስ ጣቢያ ከደረሱ በኋላ ያጋጠማቸውን ስታስረዳም "እዛ እንደደረስን በግዳጅ ቪዲዮ እንድንቀረፅ ሲደረግ ‹…ኢትዮጵያ ሀገሬ የደፈረሽ ይውደም› የሚለውን ዜማ እየዘመርን ተቀረፅን፡፡ ከዛም በግዳጅ ቃል እንድንሰጥ ደህንነቶች አስፈራሩን፤ ሁሉም ሰው የሚጠየቀው ብሔሩን በግዳጅ እንዲናገር ነበር፡፡ ብሔራችን ኢትዮጵያዊ ነው ስንል አፃያፊ ስድቦችን ይሰድቡን ነበር፡፡ ይባስ ብለውም የፌስቡክ ፓስወርዳችንን በግድ እንድንሰጣቸው አድርገውናል " በማለት የተፈፀመባትን ኢሰብአዊ ድርጊት አብራርታለች፡፡ ወጣት እየሩሳሌም የታሰሩት ሰልፈኖች ተደብድበው እያነከሱ በደም ተለውሰው ከምርመራ ክፍል ሲወጡ መመልከቷን ጨምራ ገልፃለች፡፡

ወጣት ጋሻው መርሻ ይባላል የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር የጉለሌ ክ/ከተማ አመራር ነው፡፡ ጋሻውም እንደቀደሙት የማህበሩ አመራሮች ሁሉ በፀረፋሺስት ሰልፉ ላይ ተሳትፏል፡፡ ጋሻው ከተቃውሞ ሰልፉ ጋር በተገናኘም ከሚሰራበት የመንግስት መስሪያቤት እንዲባረር ተደርጓል፡፡ ጋሻው በሰልፉ ዕለት ባይታሰርም በነጋታው (መጋቢት 9) ከስራ ገበታው ላይ ተይዞ ወደ እስር ቤት ተወስዷል፡፡ "በሰልፉ እለት አልታሰርኩም ሆኖም በነጋታው በአንድ የቀበሌ ካድሬ ጠቋሚነት ፖሊሶች ያለ መጥሪያ ከስራ ገበታዬ ላይ ይዘው ወደ እስር ወስደውኛል፡፡" የሚለው ጋሻው ከሌሎቹ ታሳሪዎች የተለየ የደረሰበት በደል እንዳለ ተጠይቆም "መጋቢት አስራአንድ በግምት ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ተኩል ሲሆን ሰልፍ በመውጣታችን ለእስር መዳረጋችንን በሚገልፅ ሁኔታ ያዘጋጀሁትን ማስታወሻ በፌስቡክ ለመልቀቅ ወይም በጋዜጣ ለማውጣት በኮምፒውተር ላይ በመተየብ ላይ እያለሁ ‹ሀገር የሚያናውጥ ጽሁፍ እያዘጋጀ ነው› ብለው ዳግም ሊይዙኝ ችለዋል" ብሏል፡፡ ወጣት ጋሻው ለዳግም እስር ከመወሰዱ አስቀድሞ ‹ሀገር የሚያናውጥ ጽሁፍ› እንዳልጻፈ በመግለፅ ሊይዙት የመጡትን አካላት ጽሁፉን እንዲያነቡት ቢጠይቅም የሚሰማው አላገኘም፡፡ ጋሻው እንደመጀመሪያው እስሩ በጣቢያዋስ አልወጣም ይልቁኑም አመፅ ቀስቃሽ ጽሁፍ አዘጋጅቷል ተብሎ ፍርድ ቤት ቀረበ፡፡ "ፍርድ ቤት ቀርቤ ነበር በምፈለግበት በማንኛውም ጊዜ እንድቀርብ ተነግሮኝ 950 ብር አስይዤ ወጥቻለሁ" የሚለው ወጣት ከፍርድ ቤት ውሎው ማግስት ወደ መስሪያ ቤቱ ሲገባ መልካም ነገር አላጋጠመውም፤ በአንዲት ፖስታ በተከተተች ወረቀት ከስራው እንደተባረረ ተነግሮታል፡፡ ጋሻው ለእስር ያበቃው ማስታወሻው "እኛስ ሀገራችን የት ነው?" የሚል ነው፤ እውነት ግን ኢትዮጵያውያን ሀገራችን የት ነው?

# በአፋር የተከሰተው ርሃብ ተባብሷል

## -የሟቾች ቁጥር 22 ደርሷል

በክልሉ ዞን ሁለት አሚባራ ወረዳን ጨምሮ በዞን አንድ በሚገኙት ኤረርሲ፣ ኤልዳዓልና ቢሩ ወረዳዎች የተከሰተው ርሃብ ተባብሶ በመቀጠሉ የሟቾች ቁጥር እያሻቀበ መሄዱን ምንጮቻችን በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ገልፀዋል:: በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ አፋር ክልል በተከሰተው በዚህ ርሃብ የሟቾች ቁጥር 22 መድረሱ ተሰምቷል::

የአፋር ክልል የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የስራ ሂደት ሃላፊ የሆኑት አቶ መሐመድ ያዮ ርሃብ በአካባቢው ጠረፋማ ወረዳዎች የተከሰተው በዋነኝነት በውሃ እጥረት ቢሆንም የምግብ እጥረቱም አለ:: የክልሉ መንግስት 2 ሚሊዮን ብር በመመደብ ውሃ በቦቴ ተሽከርካሪ እየወሰደ ለአካባቢው ማኅበረሰብ እያደረሰ ነው፣ ምግብ ግን በበቂ ሁኔታ በመጋዘናች ተከማችቶ የሚገኝ በመሆኑ እየተሰጣቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በአካባቢው ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የበሰሉ አልሚ ምግቦችን እያዳረሱ ነው:: በአሁን ወቅት ግን በአካባቢው ዝናብ በመዝነቡ የውሃውን እጥረት ችግር መቀረፉንም ጨምረው ገልፀዋል::

ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳቱን የውሃና የምግብ እጥረት ችግር ለመቅረፍ አጎራባች የአማራ ክልል ወረዳዎች ጥሩ ትብብር እያደረጉልን ቢሆንም አብዛኛው አጎራባች ቦታ ተክሎች ተተክለው በአጥር በመከለሉ ለፀጥታ ችግር ሊፈጥር ይችላል በሚል ማሳሰቡ እንዳልቀረ ገልፀውልናል::

የግብርና ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ ታረቀኝ ፅጌ በበኩላቸው በሶማሌና አፋር በተለያየ ጊዜ ድርቅ ስለሚከሰት በቂ የሆነ የምግብ ክምችት ስላለን ወደ ስፍራው ተልኳል:: የተከሰተውም ድርቅ እንጂ ርሃብ አይደልም ሲሉ አክለዋል::

ሆኖም ለፍኖተ ነፃነት የሚደርሱ መረጃዎች እንዳመለከቱት ከሆነ በአካባቢው ያለው ርሃብ እየተባባሰ ወደ አጎራባች ወረዳዎችም ተዛምቷል:: ፍኖተ ነፃነት ባለፈው ሳምንት በክልሉ ዞን አንድ ቢሩና ኤልዳዓል ወረዳ በተከሰተው ርሃብ የ 7 ሰዎች መሞታቸውን መዘገቧ የሚታወስ ሲሆን አሁን ግን ኤረርሲ የሚባል ሌላ ወረዳም ችግሩ በመከሰቱ የሟቾች ቁጥር ወደ 20 መድረሱ ተጠቁሟል::

# ሲአን ከምርጫው ለመውጣት መቃረቡን አስታወቀ

በሚቀጥለው ሚያዚያ ወር ውስጥ በሚደረገው የአካባቢ ምርጫ ለመሳተፍ ተመዝግቦ የምርጫ ምልክቱን ወስዶ እጩዎችን አስመዝግቦ በዝግጅት ላይ የሚገኘው የሲዳማ አርነት ንቅናቄ/ሲአን/ በሚደርስበት ጫና ከምርጫ ለመውጣት መቃረቡን አስታወቀ::

ሲአን ይህንን ያስታወቀው ለሲዳማ ዞንና ለሀዋሳ ከተማ ምርጫ ክልል ጽ/ቤት በላከው ደብዳቤ ነው:: በደብዳቤ ቁጥር ሲአን/116/05 መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተጽፎ በፓርቲው ሊቀመንበር በዶ/ር ሚሊዮን ቱማቶ የተፈረመው ደብዳቤ እንደሚለው "ፓርቲያችን በደረሰበት በደልና ጫና የተነሳ የመጨረሻ እርምጃ ለመውሰድ መቃረቡን መግለጽ ያመለክታል" በሚል ርዕስ አስጠንቅቋል::

ደብዳቤው በመግቢያው ላይ እንደሚገልፀው "ፓርቲያችን በፊታችን የሚደረገውን ምርጫ አንስቶ መታገስ የማይችለው በደልና ጫና እየደረሰበት በትዕግስት ጉዳዩን ለወረደና ለዞን ምርጫ ክልል ጽ/ቤቶችና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ጋራ ምክር ቤት እያመለከተን ቆይተናል:: እጩ ተወዳዳሪዎቻችንን በገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ይታሰራሉ::" በማለት ይጀምራል:: ደረሰብኝ የሚለውን ችግር ሲዘረዝርም "እጩዎቻችንን በሌሊት እያሳደደ፣እያስፈራራ፣ከስራ በማፈናቀል፣ደመወዝ በመከልከል፣በማሰር ወዘተ ከእጩነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ጫና መፍጠር፣ ስብሰባዎችን በሀይል መበተን፣የፓርሪያነችንን ባንድራ በመቀደድ ቢሮአችንን ሰብሮ በመግባት ንብረት መዝረፍ፣የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ፊልም በየገጠሩ እየዞሩ እያሳዩ አባሎቻችንን እያስፈራሩ በደም የመጣ ስልጣን በካርድ አይሞከርም ሲአንን ክዳችሁ ከአባነትና ከእጩነት ልቀቁ አለበለዝያ ደማችሁ ይፈሳል በማለት መዛት፣በየቀበሌው ልዩ ልዩ ስልጠና በመስጠት አባሎቻችንን ለማሸበር የመደቧቸው ታጣቂዎች መሳሪያ ታጥቀው በአደባባይ አባሎቻችንን በሰደፍ እየቀጠቀጡ አጠናክረው መቀጠል፣ እያስፈራሩ ከአባሎቻችን እጅ ድምጽ መስጫ ካርድ መቀማት ወዘተ ተፈጽሞብናል:: እነዚህ ችግሮችን ገዢ ፓርቲ እየፈጸመ ያለው ህዝቡ ተቆጥቶ ወደ ግጭት እንዲያመራ ሆን ብሎ የዘየደው ስልት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: ስለዚህ የዞኑ ምርጫ ክልል ጽ/ቤት ለእነዚህ ችግሮች የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲሰጠን በቀን 09/07/05 ዓ/ም በጽ/ቤት በአካል ቀርበን በቃል መጠየቃችን የሚታወቅ መሄኑን እየገለጽን ይህ ባይሆን ግን ነጻና ሰላማዊ ምርጫ ይደረጋል ብለን ወደ ምርጫ በመግባታችን በአባሎቻችንና በእጩዎቻችን ላይ እስከ ዛሬ የደረሰው እስራት፣ግድያ፣ድብደባ፣አስገድዶ ከእጩነት ማግለልና ከስራ ማፈናቀል ቀጥሎ ህዝባችን በቁጣ ወደ ሌላ አቅጣጫ ገብቶ በሰራዊት እንዳይመታ እድል ላለመስጠት ስንል ከምርጫ ለመውጣት እንደምንገደድ እየገለጽን ይህ አቤቱታ ለዚህ ጽ/ቤት የመጨረሻ መሆኑን ጭምር ለመግለጽ እንወዳለን::" ይላል::

# አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል

እርስዎም ፡-

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ

0933-89-17-66 እና

0933-89-17-67 ይደውሉ

udjparty@gmail.com

## ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ